የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሠላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፹፪
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No.82
Addis Ababa 28th Jun, 2024


ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፻፸፪/፪ሺ፲፮
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲኒማ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ

ገፅ.............................................. ፫ሺ፯፻፲


CONTENT


REGULATION NO. 172/2024
REGULATION ISSUED TO RE-ESTABLISH ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT CINEMA HOUSING ADMINISTRATION ENTERPRISE
PAGE ………………….……..……………… 3710


## ደንብ ቁጥር ፻፸፪/፪ሺ፲፮
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲኒማ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ ሲኒማ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ቀደም ሲል ሲሰራበት በነበረው የመንግስት ልማት ድርጅቶች ደንብ መሠረት ተቋቁሞ በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን የቆየ ቢሆንም ሳይንሳዊ የአሰራር ሥርዓትን መሰረት አድርጎ ያልተደራጀ በመሆኑ እና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን ከወጣው ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፲፮ ጋር ማጣጣም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ፊልም የማህበረሰባችንን አንድነትንና መልካም እሴቶችን ከማጠናከርና ከማልማት አንፃር የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛነትን በመረዳት እና የባህል እሴቶችን ለከተማው ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ፋይዳ የሚኖራቸውን ድርሻ ለማሳደግ እና ተወዳዳሪ ድርጅት እንዲሆን ለማስቻል፤

## REGULATION No. 172/2024
## REGULATION ISSUED TO RE-ESTABLISH ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT CINEMA HOUSING ADMINISTRATION ENTERPRISE

**WHEREAS,** it has become necessary to align with Regulation No. 159/2016, issued by the Addis Ababa City Administration and The Addis Ababa City Cinemas Administration enterprises was established in accordance with the government public enterprises regulations that it was previously working in and has been performing many activities, but it has not been organized based on a scientific operating system;

**WHEREAS,** to the enhancement of cultural values that yield economic, political, and social advantages for the city, thereby fostering its competitiveness and Films contribute recognizing the significance of film in reinforcing and developing unity and positive values within our society is crucial;


ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሠን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ አንቀጽ ፷፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና አንቀጽ ፺፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲኒማ ቤቶች አስተዳደር ድርጅትን እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፸፪/፪ሺ፲፮ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ደንብ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፲፮ ነው፤

፪. **"ቦርድ"** ማለት በደንቡ መሠረት የሚቋቋም የድርጅቱ አንድ የሥልጣን አካል ነው፤

፫. **"ፊልም"** ማለት ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በመጠቀም ልምድን፣ ሀሳብን፣ ስሜትን፣ ውበትን ወይም ድባብን የሚያስተላልፍ የእይታ ጥበብ ሥራ ነው፤

፬. **"የፊልም ሥራ"** ማለት ፊልም መቅረፅ፣ ማምረት፣ ማስመጣት፣ ማከፋፈል፣ ማሳየት እና መሸጥን ያጠቃልላል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለድርጅቱ መቋቋምና ዓላማ

### ፫. መቋቋም

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲኒማ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የልማት ድርጅት ሆኖ እንደገና በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. የድርጅቱ ተጠሪነት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለሥልጣን ይሆናል፤

**NOW, THEREFORE**, in accordance with sub Article (2) of Article 68 and sub Article (1) of Article 93 the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 84/2023, the Cabinet of Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This regulation may be cited as "Regulation issued to Re- Establish Addis Ababa City Government Cinema Housing Administration Enterprise Regulation No. 172/2024''.

### 2. Definition

In this regulation, unless the context otherwise requires:

1. "**Regulation**" shall mean the Regulation issued to Determine, Redefine and Lead the conditions of Public Enterprise of Addis Ababa City Administration Regulation No. 159/2024;
2. "**Board**" shall mean a body of authority of the Enterprise established in accordance with the Regulation;
3. **"Film"** means as a work of visual art that communicates experiences, ideas, emotions, beauty, or atmosphere through the medium of moving images.
4. **"Film work"** means encompasses the processes of filming, producing, importing, distributing, exhibiting, and selling films.

## PART TWO
## THE ESTABLISHMENT AND OBJECTIVE OF THE ENTERPRISE

### 3. Establishment

1. Addis Ababa City Government Cinema Housing Administration Enterprise (hereafter referred to as " Enterprise ") has been re-established as a Public Enterprise by this regulation;
2. The Enterprise 's Accountability will be to the Administration Authority of Government Public Enterprises of the Addis Ababa City Administration;

፫. ድርጅቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው ደንብ ቁጥር ፩፻፶፱/፪ሺ፲፮ መሠረት ይተዳደራል፡፡

፬. **<u>የድርጅቱ ዓላማ</u>**

ድርጅቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. በከተማው ውስጥ ለህብረተሰቡ አዝናኝና አስተማሪ የሆኑ የፊልም ትርዒቶችን ያቀርባል፣

፪. በከተማው ውስጥ ሲኒማ ቤቶችን ያደራጃል፣ ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፣

፫. ለትርዒት የሚውሉ ፊልሞችን ከውጭ ሃገር ያስመጣል፣ ያከፋፍላል፣

፬. አዋጪነቱ በጥናት ሲረጋገጥ ፊልሞችን ያመርታል፣ ከኢንርፕራይዞች ጋር በትብብር ይሰራል፣ ለሀገር ውስጥና ለዓለም አቀፍ ገበያ ያቀርባል፣

፭. አዋጪነቱ በጥናት ሲረጋገጥ የፊልም ፌስቲቫል ያዘጋጃል፣ አለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ፌስቲቫል ላይ ይሳተፋል::

፮. ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ይተምናል፣

፯. ከፊልም ሥራዎች ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሌሎች ሥራዎችን ይሰራል፡፡

፭. **<u>ድርጅቱ እንዲያቀርብ የሚጠበቅበት የሕዝብ አገልግሎት ግዴታ</u>**

በከተማው ውስጥ የተለያዩ በጎ አድራጎት ተግባራት ላይ መሳተፍ፡፡

፮. **<u>ካፒታል</u>**

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፩ ቢሊዮን ፮፻ ሚሊዮን፣ ፩፻፴፫ሺ፣ ፱፻፩ (አንድ ቢሊዮን ስድስት መቶ ሚሊዮን አንድ መቶ ሠላሳ ሦስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አንድ ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፩ ቢሊዮን ፭፻፸፮ ሚሊዮን፣ ፩፻፴፫ሺ፣ ፱፻፩ (አንድ ቢሊዮን አምስት መቶ ሰባ ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሠላሳ ሦስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አንድ ብር) በዓይነት እና ፳፬ ሚሊዮን (ሃያ አራት ሚሊየን) በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል፡፡

፯. **<u>ኃላፊነት</u>**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

3. The Enterprise is administered in accordance with the Regulation issued to Determine, Redefine and Lead the Conditions of Public Enterprise of Addis Ababa City Administration Regulation No. 159/2024.

4. **<u>Objective of the Enterprise</u>**

The Enterprise shall have the following Objectives:-

1. Stage creational and educational film shows in the City.
2. organize, promote and manage cinema houses in the City;
3. import and distribute films to be designated for shows';
4. Produces films when proven by feasibility research and it works in collaboration with enterprises. Supply to the local and international market.
5. organize a film festival and participate in both international and national festivals; If the feasibility of production is confirmed by research,
6. determine and collect changes for the service it provides.
7. carryout other activities related with film undertaking;

5. **<u>Public Service Obligation that the Enterprise is Expected to Provide</u>**

Engaging in a variety of volunteer activities across the city;

6. **<u>Capital</u>**

the authorized capital for the Enterprise is Birr 1,600,133,901.00 (one billion six hundred million one hundred thirty three thousand nine hundred and one) Birr, of which Birr 1,576,133,901.00 (One Billion five hundred seventy six million one hundred thirty three thousand nine hundred and one) Birr in kind and Birr 24,000,000 (twenty four million) Birr was paid in cash.

7. **<u>Liability</u>**

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

፰. **ዋና መስሪያ ቤት**

የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በከተማው ክልል ውስጥ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

፱. **ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለሥልጣን የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

፲. **የድርጅቱ አደረጃጀት**

ድርጅቱ

፩. የሥራ አመራር ቦርድ፤

፪. አንድ ዋና ሥራ አስፈጸሚ እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች፤

፫. ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

፲፩. **ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

፲፪. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም. ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም.**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

8. **The Head Office**

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa, and may have branch offices elsewhere in other parts of the city as may be necessary.

9. **Supervisory Authority**

Addis Ababa City Administration Public Enterprise Administration Authority shall be the Enterprise's Supervisory Authority.

10. **Organizational Structure**

The enterprise shall have:

1. Management Board of the Enterprise;
2. A Chief Executive Officer and Deputy Chief Executive Officers as necessary and;
3. The necessary staff.

11. **Duration of the Enterprise**

The Enterprise is established for an indefinite period of duration.

12. **Effective Date**

This regulation shall enter into force as of this 28 day of June, 2024.

**Done at Addis Ababa, this 28th day of June 2024.**

**ADANECH ABEBE DESA**

**MAYOR OF ADDIS ABABA**